# የራሷ እያረረ
# <u>የሰው ስታማስል</u>

ተፈጥሮ ቢሆንም ፣ መውደድና መጥላት
የገጠመን እኛ ፣ ወዳጅ ሲሏት ፣ ጠላት
ልቧ የማይገኝ ፣ ጋባዥ ለደምፍላት
የለዘበች ሰይጣን ፣ አቻ አልተገኘላት ።

ለውጥ ለውጥ ፣ ትላለች ፣ ሳትለወጥ እሷ
ቅቤ እየጠበሰች ፣ ባሳሳች ምልሷ
ልዩ አጀንዳ ይዛ ፣ ሸሸጋ ለራሷ
ለካስ ፣ ኬኛ ኬኛ ፣ ነበረ ጥንስሷ ።

ከወያኔ አትከፋም ፣ ብሎ ቢቀበላት
ከነ ግሳንግሷ ፣ ተሸክሞ ቢያዝላት
ሚሊዮን ፣ ልትሸውድ ፣ በጠባብ ጭንቅላት
እሷ ፣ ብቻ አዋቂ ፣ የሆነች መሰላት
　　　　ፀበል አትወሰድ ፣ እምነቷ አይፈቅድላት
　　　　አቶ እስራኤል ዳንሳ ፣ ምነው ብትደርስላት ።

እቺን ምናምቴ ፣ እቺን የወሬ ቋት
ገመዱ ቢረዝም ፣ መስሏት የለቀቋት
ፊት እየነሳችሁ ፣ ምናል ብታርቋት
ለኛም አታሳዩን ፣ በሸሻ ደብቋት ።

ኬኛ ኬኛ ፣ የምትል ፣ ሲመሽ ፣ በሯን ዘግታ
የሰው ስጋ በልታ ፣ የሰው ደም ጠጥታ
የማትጠረቃ ፣ አታውቅ ከበሬታ
እንደ ለገጣፎ ፣ ዛሬም በሱሉልታ
ተነስታለች ዳግም ፣ የሌላት ይሉኝታ
　　　　ይሄንንም አላውቅ ፣ ትለናለች ወጥታ
　　　　አለልክ ተብታ ፣ ከቶ ፣ ማንን ፈርታ ።

እሳት ተቀጣጥሎ ፣ ባህርዳር መቀሌ
አንዴ ከኬኒያ ፣ አንዴ ከሱማሌ
የምታቶሶትስ ፣ የመንደር አለሌ
ምነው ፣ ሃይ የሚላት ፣ ጠፋ ሽማግሌ ።

የሰላም ያንድነት ፣ ፊታውራሪ ይመስል
ወሬ እያራገበች ፣ የምትል ፣ ጡል ጡል
የራሷ እያረረ ፣ የሰው ስታማስል
ታውደለድላለች ፣ ወጧ ፣ ያማረ ይመስል ።

ታዛቢው

March 15, 2019